March 26, 2019 QuickNotes

## ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም (Summer RISE Program) የተማሪዎች ምዝገባ ተጀምሯል

Summer RISE ለተማሪዎች የሦስት ሣምንት በሙያ ላይ የተመሰረተ የትምህርት ተሞክሮ በማቅረብ እና ተማሪዎች ከፍላጎታቸው ጋር የሚስማማ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያላቸው የሙያ አማራጮች ጋር ያስተዋውቃል። ማርች 27 እኩለ ሌሊት ላይ የተማሪዎች ምዝገባ ይጠናቀቃል።

ስለ Summer RISE ይበልጥ መረጃ ለማግኘት እና በተሳታፊነት ለመመዝገብ እዚህ ይጫኑ።

## የባጀት ዓመት 2020 የ MCPS የሥራ ማስኬጃ ባጀት አስተያየት ወቅታዊ መረጃ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ሥራ አስፈጻሚ Marc Elrich ለባጀት ዓመት (FY) 2020 አስተያየት የተሰጠበትን የሥራ ማስኬጃ ባጀት $5.7 billion/ቢሊዮን ማርች 15 አቅርበዋል። ባጀቱ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ $2.6 billion/ቢሊዮን ያካትታል፣ ይኼውም ከስቴቱ ጥረትን የመደገፍ ደረጃ $2.5 million/ሚሊዮን አብላጫ ቢኖረውም ነገር ግን የትምህርት ቦርድ ካቀረበው የባጀት ጥያቄ በ $14.5 million/ሚሊዮን ያንሳል።

የካውንቲው ሥራ አስፈጻሚ Marc Elrich ስላቀረቡት የበጀት ዓመት FY 20 የሥራ ማስኬጃ ባጀት፤ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፕሬዚደንት Shebra Evans እና ሱፐርኢንተንደንት Jack Smith የሚከተለውን መግለጫ ሰጥተዋል

> "የካውንቲ ሥራ አስፈጻሚ Elrich ጥረትን ከመደገፍ አብላጫ ጭምር በትምህርት ቤቶቻችን ኢንቨስት በማድረጋቸው እናመሰግናለን። ምንም እንኳ ካውንቲያችን የገቢ ተግዳሮት ቢደቀንበትም፣ የነገውን ኢኮኖሚ ለመገንባት በተማሪዎቻችን ላይ ኢንቨስት ማድረግ ያለብን አሁን መሆኑን Mr. Elrich ይረዳሉ። በካውንቲያችን የገቢ ሁኔታ ከታቀደው በታች እየቀነሰ ቢሄድም፣ MCPS የፋይናንስ ኃላፊነት በተሞላበት አጠቃቀም አጋር ለመሆን ቁርጠኛ ነው። "ይህ ባጀት በሚዘጋጅበት ወቅት የትምህርት ዲስትሪክት መሪዎች ከካውንቲ የሥራ አስፈጻሚ ጽ/ቤት ጋር በትብብር ሠርተዋል። ይህ ባጀት ቦርዱ የጠየቀየውን ያህል የማያሟላ ቢሆንም፣ ቅድመ ሙዓለህፃናት ማስፋፋትን ጨምሮ፣ቅድሚያ የምንሰጣቸዉ የሚያነሳሱንን ውጥኖቻችንን ማሟላት እንደምንችል እናምናለን። ቢሆንም ግን፣ በእቅድ የያዝናቸውን አንዳንዶቹን መቀነስ እና ሌሎቹን ማዘግየት ይኖርብናል።
>
> "በሚቀጥሉት ሁለት ወራት፣ በመጀመሪያ የባጀት ጥያቄያችን መሠረት ማስተካከያ የማድረግ እድሎች ይኖሩ እንደሆነ ለመወሰን እና በቅነሳው ምክንያት በተማሪዎች እና በት/ቤቶች ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ ለመቀነስ ከካውንቲ ካውንስል አጋሮቻችን ጋር አብረን እንሰራለን።
>
> "ስለ 2020-2021 የትምህርት ዓመት የሥራ ማስኬጃ ባጀት አሻግረን እየተመለከትን፣ በቀጠሮ ወይም በይደር የሚገኘውን ከ Kirwan legislation/ደንብ ጋር እንዲጣጣም እና ተማሪዎቻችንን ለማገልገል

በምናደረገው ያላሰለሰ ጥረት MCPS በጣም ብቃት ያላቸውን ግብረኃይል ለመቅጠር እና ለማቆየት እንድንችል ለካውንቲያችን መሪዎች እጅግ ከፍ ያለ የገንዘብ/ፈንድ ጥያቄ እንደምናቀርብ እንገምታለን።

ለባጀት ዓመት (FY) 2020 ፌብሩዋሪ ላይ የትምህርት ቦርድ $2.66 billion/ቢሊዮን የሥራ ማስኬጃ ባጀት በሙሉ ድምፅ አጽድቋል። ይህም MCPS የ 2019-2020 የትምህርት ዓመትን ፈንድ የሚያደርግበት የ $25 million ባጀት በዚህ ዓመት ለመቆጠብ እንዲያስችለን በካውንቲው የቁጠባዎች እቅድ መሣተፍን ያካትታል።

ይመልከቱባጀቱን

ባጀቱ የዲስትሪክቱን ጥረት ለማሻሻልና ለማጠንከር አስፈላጊ የሆኑ ቁልፍ የሥራ ፕሮግራሞችን፤ ጠንካራ የአካደሚክ እና የሥራ እድሎች ተደራሽነትን ለመጨመር፤ትምህርትን ለማስፋፋት፤ የቋንቋ እድሎችን ለመስጠት፤ በአካላዊ፣ማህበራዊ እና ስነልቦናዊ የተሟላ ደህንነት ላይ ለማተኮር፤ ውጤታማ የሆኑ ብዝሃነት ያለው የሥራ ግብረኃይል ለመቅጠርና ለማቆየት፣ እና የተግባር ጥንካሬን ማጎልበትን ያካትታል። ይኼውም ለሚከተሉት ፈንድ ማድረግን ያካትታል፦

- የክፍል መጠንን መቀነስ መመሪያዎች
- የቅድመ ሙዓለህፃናት ፕሮግራሞችን ማስፋፋት
- ለመመረቅ አማራጭ/ተተኪ መንገዶችን መፍጠር
- በትምህርት ቤቶች የመሪነት ደረጃዎችን መጨመር
- ለልዩ ትምህርት እና እንግሊዝኛ ሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎች (ESOL) ተማሪዎች ልዩ/የተለየ እና የፕሮግራም ድጋፍ መስጠት
- በሁለት የኤለመንተሪ ት/ቤቶች የተራዘመ ዓመት ፕሮግራም መተግበር
- ለተማሪ የአካል፣ ማህበራዊ እና ስነልቦናዊ የተሟላ ደህንነት ፕሮግራሞችን እና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን መጨመር
- በሞንትጎመሪ ኮሌጅ ለተማሪዎች የሁለትዮሽ-ምዝገባ እድሎችን ማስፋፋት
- ለተማሪዎች የሠመር ራይዝ (Summer RISE) የሙያ ሥራ ዳሰሳ ፕሮግራም ማስፋፋት
- የትምህርት ቤት ሠላምና ደህንነት እና የተማሪ ደህንነት እርምጃዎችን ሥርዓት ማጠንከር
- ለሠራተኞች የሙያ ሥራ መንገዶችን እና የሙያ ማበልፀጊያ እድሎችን ማስፋፋት
- የሙያ ማሳደጊያ/ማዳበሪያ መድረኮችን ለማስፋፋት እና ለትምህርት ቤቶች ድጋፍ ለመስጠት የቴክኖሎጂ ማሻሻያዎችን መጨመር

ቦርዱ ያፀደቀው የሥራ ማስኬጃ ባጃት በየዘርፉ ካሉት የባለድርሻ አካላት፣ ሠራተኞችን ጭምር፣ ወላጆች፣

ተማሪዎች እና የማህበረሰብ አባላትን አስተዋጽኦ ያንፀባርቃል።

**የጨቅላ ወጣት ፍቅረኛሞችን ግጭት የሚገመግም "መከባበርን መምረጥ - Choose Respect" ኮንፈረንስ**

10ኛው ዓመታዊ Choose Respect Montgomery Conference እሁድ፣ ኤፕሪል 7 በሪቻርድ ሞንትጎመሪ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት - Richard Montgomery High School ይካሄዳል። የለጋ ወጣት ፍቅረኛሞች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶች ዙርያ የሚመረምረው ይህ ሁነት፣ ከ 12:30–1:30 p.m. የሚካሄድ የሪሶርስ አውደርእይ ያካትታል። ኮንፈረንሱ ለተማሪዎች፣ ለወላጆች፣ ለትምህርት ባለሙያዎች እና ለወጣቶች የአገልግሎት ሰጪዎች ከ 1:30–5 p.m. እርስበርስ አሳታፊ አውደጥናቶችን ይጨምራል።

ይህ ኮንፈረንስ በፍቅረኛሞች ውሎ ዙርያ የሚከሰቱ አግባብነት የሌላቸው ጉዳዮችን ይመረምራል። በ ዩ.ኤስ. ከሦስት ታዳጊ ወጣት ዉስጥ አንዱ/ዷ ከፍቅር አጋሯ/ሩ የአካላዊ፣ ጾታዊ፣ ስሜታዊ ወይም የቃላት ጥቃት ሰለባ ነዉ/ናት። ይህ ቁጥር ከሌላ አይነት የወጣቶች ግጭት መጠን በእጅጉ ይበልጣል። በአገር አቀፍ ደረጃ በአንድ ዓመት ውስጥ እስከ 1.5 ሚሊዮን ያህል የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ከፍቅረኛ ጓደኞቻቸው ጥቃት ይደርስባቸዋል።

እዚህ ይመዝገቡ።

**ለ 2019 የሙያ ሥራ ዝግጁነት የሠመር ካምፕ ምዝገባ አሁን ክፍት ነው**

በሮቦቲክስ (robotics)፣ በምህንድስና (engineering)፣ ወይም በምግብ አዘገጃጀት ጥበብ (culinary arts) ፍላጎት ያለው/ያላት የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ አለዎት-አለችዎት? በተሽከርካሪዎች/አውቶሞቲቭ ወይስ በኮምፒውተሮች መሥራት ይወዳሉ? ለ 2019 የሙያ ሥራ ዝግጁነት የሠመር ካምፕ ምዝገባ አሁን ክፍት ነው! ካምፖቹ ከጁን 24 - 28 በጌትስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Gaithersburg High School) እና በቶማስ ኤዲሰን ሁለተኛ ደረጃ ቴክኖሎጂ ት/ቤት (Thomas Edison High School of Technology) ከጁላይ 8 - 12 ይካሄዳሉ። የ 2019 ካምፕ የሙያ ሥራ ዝግጁነት ካምፕ የሚሰጣቸውን እዚህ ይመልከቱ። ዋጋው ለእያንዳንዱ ተማሪ $50/ለአንድ ካምፕ ሲሆን መስፈርት ለሚያሟሉ ተማሪዎች ቅናሽ የፋይናንስ ድጋፍ ይኖራል።

ለምዝገባ https://goo.gl/VEaWQf ይጎብኙ።

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ ይህንን ድረ-ገጽ ይጎብኙ።

**የፍትኃዊ ተሐድሶ አውደጥናት ኤፐሪል 2 ይካሄዳል**

ሠራተኞች፣ ወላጆች፣ ሞግዚቶች እና የማህበረሰብ አባላት ማክሰኞ ኤፐሪል 2 በ A. Mario Loiederman መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ከ 6:30–8 p.m. በሚካሄደው ስለ ዲስትሪክቱ ፍትኃዊ ተሐድሶ ራዕይ እና ይኼ የማህበራዊ ፍትህ መድረክ እንዴት ተማሪዎች በንቃት እንዲሣተፉ እና ፐሮብሌምን ማቃለል በህይወታቸዉ ላይ እና በአጠቃላይ ህብረተሰቡ ላይ ተጽእኖ የሚያሳደሩ አካላዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ማህበራዊ እና የስነምግባር ጉዳዮች ይበልጥ ለመማር በሚያስችል አውደጥናት ላይ እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል።

የ ሎይደርማን/Loiederman አድራሻ፡- 12701 Goodhill Road, Silver Spring

RSVP/እዚህ ይመዝገቡ። የበለጠ መረጃ ለማግኘት የስልክ ቁጥር፡- 240-740-3951 ይደውሉ።

**ምስል የተለጠፈበት ማስታወቂያ/ፖስተር ውድድር ለሠራተኞች እና ለተማሪዎች ተከፍቷል**

የፈጠራ ችሎታህን/ሽን ለማፍለቅ ተዘጋጅ/ጂ! የትምህርት ቤት የኃይል እና እንደገና በጥቅም ላይ የሚያውል ቡድን (SERT) ለኤለመንተሪ፣ መካከለኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ... እና ሠራተኞች ምስል የተለጠፈበት ማስታወቂያ/ፖስተር ዓመታዊ ውድድሩን ያካሄዳል።

የ "Watt's Up poster" ውድድር ለሠራተኞች ወይም K–12 ለሚማሩ ተማሪዎች ክፍት ሲሆን ፈጠራው ኃይልን የመቆጠብ እና እንደገና ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ ኃላፊነት እንዲወስዱ ሌሎችን በማደፋፈር ላይ ያተኮረ መሆን አለበት። የዚህ ዓመት መሪ ቃል "SERT In Our School" የሚል ነው። የአንተ/ቺ ትምህርት ቤት "አረንጓዴ/green" ለመሆን ምን እንደሚያደርግ ለሌሎች አሳይ/ግለጽ (ጨ)። **ለውድድሩ ማስገቢያ ገደብ ሰኞ፣ ኤፐሪል 1 ነው።**

የውድድሩ አሸናፊ ግቤቶች/entries ወደፊት በ MCPS እና በአካባቢ የመንግስት ትምህርታዊ ወይም የማስተዋወቅ ዘመቻዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። መወዳደሪያዎቹን ለ Watt's up? ውድድር ይላኩ። Montgomery County Public Schools, 45 W. Gude Dr., Suite 4000, Rockville, MD 20850

ተጨማሪ መረጃ እዚህ ይገኛል።

Watt's Up Entry Form

**የወጣት ሴት ጉልበት/Girl Power የድርሰት ውድድር ምዝገባ እስከ ማርች 30 ይቀበላል**

የሴቶችን ታሪካዊ ወር ለማክበር የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሴቶች ኮሚሽን በሦስተኛው ዓመታዊ "Girl Power" ውድድር እንዲሳተፉ ነዋሪዎችን ይጋብዛል። መወዳደሪያዎቹ "የልዕለ ኃያልነት ሥልጣን ቢኖርህ/ሽ፣ ልጃገረዶችን እና ሴቶችን ለመርዳት ሥልጣንህ(ሽ)ን እንዴት ትጠቀምበታለህ/ትጠቀሚበታለሽ/If you had a superpower, how would you use that power to help girls and women?" ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ የሚሰጡ መሆን አለባቸው።

ከ 5 እስከ 105 ዓመት እድሜ መካከል ያሉ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪዎች አጭር ትረካ፣ ግጥም፣ ስዕል ወይም ሌላ ማንኛዉም የውድድሩን ጭብጥ የሚመለከት ነገር እንዲያቀርቡ እናደፋፍራለን። ውድድሩ የሚወሰነው በፈጠራ ችሎታ እና በይዘት ይሆናል፤ ተወዳዳሪዎች የብልግና/አጸያፊ ነገሮችን መጠቀም እና ከዘረኝነት ወይም ጾታዊ ከሆኑ አስተያየቶች ወይም ገጽታዎች መቆጠብ ይኖርባቸዋል። ተወዳዳሪ አሸናፊዎች የሚመረጡት ከአራት ዘርፎች፡- ኤለመንተሪ፣ መካከለኛ፣ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና ከጎልማሶች ይሆናል።

ውድድሩ ስፖንሰር የሚደረገው በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሴቶች ኮሚሽን፣ሞንትጎመሪ ካውንቲ መጽሔት እና በቤተመጻሕፍት ወዳጆች ነው። በከፍተኛ ደረጃ አሸናፊ የሆኑት በሞንትጎመሪ መጽሔት ላይ ይወጣሉ። የውድድሩ አሸናፊዎች በሴቶች ኮሚሽን ድረ-ገጽ ላይ ይወጣሉ እና swag ቦርሳ ያገኛሉ፣ ከኮሚሽነሮች ጋር ፎተግራፍ መነሣት፣ እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሴቶች ኮሚሽን የአሸናፊዎች ምርጫ በክብር እንግድነት ይጋበዛሉ።

እስከ ማርች 30 ቢቀርብ ተቀባይነት አለው (ለአንድ ሰው አንድ ብቻ መወሰን አለበት)። የጽሑፍ መወዳደሪያው ከ 500 ቃላት መብለጥ የለበትም። አሸናፊዎች ኤፕሪል 30 ይፋ ይደረጋል።

የበለጠ መረጃ ለማግኘት እና በድረ-ገጽ የሚሞላ ቅጽ እዚህ ይገኛል።

የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ በስልክ ቁጥር፡- 240-777-8300 ይደውሉ ወይም ይህንን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡-
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ኮሚሽን ለሴቶች/Montgomery County Commission for Women

**ለወጣቶች ከፍተኛ አገልግሎት የ Nancy Dworkin ዓመታዊ ሽልማቶች ጥቆማዎችን ይፈልጋል**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የልጆች እና የወጣቶች ኮሚሽን ለወጣቶች ከፍተኛ አገልግሎት 33ኛ ዓመታዊ የ Nancy Dworkin ሽልማቶች ጥቆማዎችን ይፈልጋል። ሽልማቶቹ በሞንትጎመሪ ካውንቲ በልጆች እና በወጣቶች ህይወት ትርጉም ያለው ልዩነት ያመጡ ግለሰቦችን እና ድርጅቶችን እውቅና ይሰጣል።

ጥቆማዎች ማከሰኞ፣ ኤፕሪል 2 መቅረብ አለባቸው።

**የሽልማት ዘርፎች፡-**

- **ወጣት** - ልጅ ወይም ወጣት ሰው፣ 21 ዓመት ዕድሜ እና ከዚያ ያነሰ፣ ለልጆች እና ለወጣቶች አገልግሎት ያበረከተ/ች።
- **አገልግሎት ሰጪ** – ግለሰብ (ለምሳሌ፡- አስተማሪ፣ ካውንስለር፣ የፖሊስ መኰንን፣ የእሳት አደጋ ሠራተኛ) ለልጆች እና ለወጣቶች አገልግሎት የሚሰጥ/የምትሰጥ ግለሰብ።
- **በጎፈቃደኛ** - ለልጆች እና ለወጣቶች የበጎፈቃደኝነት አገልግሎቶችን የሚሰጥ/የምትሰጥ ግለሰብ።
- **ድርጅት** – ለልጆች እና ለወጣቶች አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ድርጅት።

- **ቢዝነስ –** በካውንቲው ለትርፍ የሚሠራ - ቢዝነስ ለልጆች እና ለወጣቶች የላቀ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሰጠ።

ሽልማቱ የተሰየመው በ1987 የሞቱት የቀድሞው የኮሚሽን ሊቀመንበር በነበሩት Nancy Dworkin መታሰቢያነት ነው። የተጠቋሚዎቹን አገልግሎት የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ጥቆማ ማቅረብ ይችላል/ትችላለች። ተጠቋሚዎች በሙሉ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ለልጆች እና ለወጣቶች አገልግሎት የሰጡ መሆን አለባቸው።

ጥቆማዎቹ ለ erin.stillwell@montgomerycountymd.gov በኢ-ሜይል መላክ አለባቸው ።

ለመጠቆሚያ መመሪያ ኮፒ https://bit.ly/2u9j2cG ይጎብኙ። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣
ለ Erin Stillwell በስልክ ቁጥር፡- 240-777-1716 ይደውሉ ወይም በ
erin.stillwell@montgomerycountymd.gov ኢ-ሜይል ያድርጉ።